አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

# አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ

# ADDIS NEGARI GAZETA

**OF THE CITY GOVERNMENT OF ADDIS ABABA**

**አራተኛ ዓመት ቁጥር ፹፬**
**አዲስ አበባ ታህሳስ ፲፫ ፪ሺ፰ ዓ.ም**

በአዲስ አበባ ከተማ
ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

**FOURTH YEAR NO.84**
**ADDIS ABABA JUNUARY 21ST, 2016**

## ማውጫ

**የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር**
**መናፈሻ ልማት ፕሮጀክት ጽህፈት ቤት**
**ማቋቋሚያ ደንብ...................... □□ ፩**

## Content

**Addis Ababa City Government Park**
**Development Project Office Establishment**
**Regulation………………………..…Page 1**

**ደንብ ቁ□ር ፹፬/፪ሺ፰**

**የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር**

**መናፈሻ ልማት ፕሮጀክት ጽህፈት ቤት**

**ማቋቋሚያ**

አረንጓዴ ልማት የመፍጠር ራእይ ለማሳካት ከፍተኛ ጠቀሜታ ያለው ከመሆኑም በላይ ለማህበራዊ ግንኙነት፣ ለባሕልና ስነ ጥበብ መግለጫ፣ ለምጣኔ ሃብታዊ ፋይዳ እና ለከተማዋ ጤናማ ስነ ምህዳራዊ ትስስር የሚያገለግል መሆኑ፣

**Regulation No. 84/2016**

**Addis Ababa City Government**

**Park Development Project Office Establishment**

**Regulation**

**WHEREAS**, it is found necessary that the construction of park in Addis Ababa has got great importance so as to meet the vision to create a green development and use it for social relationship, cultural and art exhibition, economic contribution and the vigorous ecological relationship of the city;

ያንዱ ዋጋ
Unit price

አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ ፪ ሺ፬፻፵፭
Addis Negari Gazeta P.O.Box 2445

በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ የኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ አንቅስቃሴዎች ከጊዜ ወደጊዜ መስፋፋት ምክንያት የተፈጥሮ አየር መዛባት፣ የመናፈሻና የአረንጓዴ ቦታዎች ዕፅዋት ሽፋን ላይ ከፍተኛ መመናመን እየ□ረሰ በመሆኑ እና የመናፈሻዎች ቁጥር እያደገ ከመጣው የህብረተሰቡ ፍላጎት ጋር ተመጣጣኝ አለመሆን የፈጠረውን ችግር መቅረፍ በማስፈለጉ፣

በተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር ፫፻፷፩/፲፱፻፺፭ አንቀጽ ፳፫/፩ (ረ) እና በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈፃሚና ማዘጋጃ ቤት አገልግሎት አካላት እንደገና ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፴፭/፪ሺ፩ በአንቀጽ ፹፬ በተሰጠው ስልጣን መሠረት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ካቢኔ ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

**፩. አ□ ር ርክስ**

ይህ ደንብ "የመናፈሻ ፕሮጀክት ልማት ጽህፈት ቤት ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር ፹፬/፪ሺ፱" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፡-

፩."**ከተማ**" ማለት የአዲስ አበባ ከተማ ነው፡፡

፪. "**አስተዳደር**" ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ነው፡፡

፫. "**ኤጀንሲ**" ማለት የአዲስ አበባ ከተማ የውበት፣ መናፈሻና ዘላቂ ማረፊያ ልማትና አስተዳደር ኤጀንሲ ነው፡፡

**WHEREAS**, it is found necessary to preclude the imbalanced number of recreational places with that of the growth of the society's demand for it; immense deterioration of the vegetation coverage of green areas and recreational places; and climate change due to the gradual expansion of the economical and social activities of the city of Addis Ababa;

**NOW, THEREFORE,** in accordance with article 23/1/f/ of the Addis Ababa city government revised charter proclamation number 361/2003, as well as article 84 of the Addis Ababa city government executive and municipal service organs re-establishment proclamation number 35/2012, the city cabinet has issued this regulation as follows.

## Part One
## General Provisions

**1. Short Title**

This regulation may be cited as "Park development project office establishment regulation number 84/2016."

**2. Definition**

In this regulation, unless the context otherwise requires:

1. "**City**" means the Addis Ababa City.
2. "**Administration**" means the Addis Ababa City administration.
3. **"Agency"** means the beautification, parks, and cemetery development and administration agency of the city of Addis Ababa.

፬. "ፕሮጀክት ጽህፈት ቤት" ማለት በዚህ ደንብ መሰረት የተቋቋመ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመናፈሻ ልማት ፕሮጀክት ጽ/ቤት ነው፡፡

፭. "ሰ□ ‑" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው::

፮. በወንድ ጾታ የተገጹ ለሴት ጾታም ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

## ፫. የተፈጻሚነት ወሰን

ይህ ደንብ በአዲስ አበባ ከተማ መናፈሻ ልማት ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡

## ክፍል ሁለት
## መቋቋም፣ ተጠሪነት፣ አደረጃጀት ስልጣንና ተፅባር

## ፬. መቋቋምና ተጠሪነት

፩. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መናፈሻ ልማት ፕሮጀክት ጽ/ቤት ከዚህ በኋላ "ፕሮጀክት ጽ/ቤት" እየተባለ የሚጠራ ህጋዊ ሰውነት ያለው አካል ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡

፪. ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ተጠሪነቱ ለኤጀንሲው ነው፡፡

## ፭. አደረጃጀት

ፕሮጀክት ጽህፈት ቤቱ፡-

፩. የስራ አመራር ቦርድ (ከዚህ በኋላ ቦርድ እየተባለ የሚጠራው)፤

፪. ዋና ስራ አስኪያጅ፤

፫. ሌሎች አስፈላጊ የስራ ክፍሎች ሰራተኞች ይኖሩታል፡፡

4. **“Project Office”** means the Addis Ababa city government park development project office which is established according to this regulation.
5. “**Person**” means any natural or juridical person.
6. Any expression in the masculine gender shall be applicable to the feminine.

## 3. Scope of Application

This regulation shall be applicable to the Addis Ababa city park development.

## Part Two
## Establishment, Accountability, Organization, Power and Duties

## 4. Establishment and Accountability

1. The Addis Ababa City Administration park development project office (here-in-after “project office”) is hereby established as an autonomous body having its own legal personality.
2. The project office shall be accountable to the agency.

## 5. Organization

The project office shall have:

1. Management board (here-in-after the “board”);
2. General Manager;
3. Other necessary staff.

**፮. ዋና መስሪያ ቤት**

የፕሮጀክት ጽህፈት ቤቱ ዋና መስሪያ ቤት በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ይሆናል፡፡

**፯. ፕሮጀክት ጽህፈት ቤቱ ስልጣንና ተግባር**

የመናፈሻ፡-

፩. ንድፈ ሃሳባዊ እና ዝርዝር ድዛይን በራሱ ወይም በጨረታ ያዘጋጃል፣ ያለማል፣ ይቆጣጠራል፣ ያስተዳድራል፣

፪. በጥናትና ምርምር በመታገዝ የልማትና አስተዳደር ሥራዎችን በበላይነት ይመራል፣ ይቆጣጠራል፣ ያስተባብራል፣

፫. ስራዎች በውሉ መሰረት መፈጸማቸውን በማረጋገጥ ክፍያ ይፈጽማል፣

፬. የውበት፣ መናፈሻና የከተማዋን አየር ሚዛን የሚጠብቁ የዛፍ ችግኞች፣ አበባና የዛፍ ዝርያዎች የሚበዙበትንና የሚስፋፉበትን ሁኔታ ያስተዳድራል፡፡

**፰. የስራ አመራር ቦርድ አሰያየም**

፩. ቦርዱ ተጠሪነቱ ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሥራ አስኪያጅ ይሆናል፡፡

፪. የስራ አመራር ቦርዱ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው መስሪያ ቤቶች የተውጣጡ ከ፯ እስከ ፱ አባላት ይኖሩታል፡፡

፫. የቦርድ ሰብሳቢውና አባላት በኤጀንሲው አቅራቢነት በከንቲባው ይሰየማል፡፡

**6. Head Office**

The head office of the project office shall be in Addis Ababa.

**7. Power and Duties of the Project Office**

For park:

1. Produce conceptual and detail design by itself or bide develop, administer and control;
2. Organize, control and lead the development and administration works based on research
3. Issue payment after the works are carried out according to the contract;
4. Expand and administer conditions for the propagation of species of tree seedlings, flowers and trees that maintain the beautification, recreation and weather balance of the city.

**8. Appointment of the Management Board**

1. The board shall be accountable to the manager of the Addis Ababa City Government.
2. The management board shall have from 7 up to 9 members drawn from the appropriate government offices related to the issue.
3. The chairperson of the board and its members shall be appointed by the mayor through their nomination by the agency.

## ፱. የቦርዱ ስልጣንና ተግባር

፩. የፕሮጀክት ጽህፈት ቤቱ የተሰጠውን ስልጣንና ተግባር በአግባቡ መወጣቱን ያረጋግጣል፡፡

፪. አግባብነት ያላቸው የህግ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ቦርዱ ፕሮጀክት ጽህፈት ቤቱን በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ ከፍተኛ ውሳኔ ሰጪ አካል ነው፡፡

፫. በፕሮጀክት ጽህፈት ቤት ዋና ስራ አስኪያጅ የሚቀርብለትን ዓመታዊ የሥራ አፈጻጸምና የበጀት አጠቃቀም ሪፖርት በኦዲት አስመርምሮ እንዲጸድቅ ያደርጋል፡፡

፬. የፕሮጀክት ጽህፈት ቤቱን ኃላፊዎችን እንዲመድቡ እና እንዳስፈላጊነቱ እንዲሰናበቱ ያደርጋል፡፡

፭. በፕሮጀክት ጽህፈት ቤቱ የሚቀርብለትን የፕሮጀክት ሰራተኞች የስራ መመሪያ ያጸድቃል፣ ክፍያዎችንም ይወስናል፣ የተመደበለትን በጀት በአግባቡ ለታለመለት ተግባር መዋሉን ይቆጣጠራል፣ የአፈጻጸም ችግሮች ላይ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

## ፲. የቦርዱ ስብሰባ

፩. ቦርዱ በወር አንድ ጊዜ መደበኛ ስብሰባ ያደርጋል፡፡

፪. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ ፩ የተጠቀሰው እንደተጠበቀው ሆኖ የቦርዱ ሰብሳቢ ወይም ከአባላቱ አንድ ሶስተኛው ከጠየቁ አስቸካይ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል፡፡

፫. የቦርድ አባላት ከግማሽ በላይ ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤ ይሆናል፡፡

## 9. Power and Duties of the Board

1. Make sure that the project office has carried out its power and duties correctly.
2. The board, without prejudice to the relevant legal provisions, shall be the highest decision making body concerning issues related to the office.
3. Scrutinize the annual work performance and budget utilization presented by the general manager of the project office through audit and verify its ratification.
4. Make sure of the appointment of the heads of the project office or their dismissal as may be necessary.
5. Approve the work directive for the project employees presented by the project office; decide payments; control whether the allocated budget is used properly for the intended task; give decisions on operational problems.

## 10. Meetings of the Board

1. The board shall convene its ordinary meeting every month.
2. Without prejudice to sub-article 1 of this article, it may hold extraordinary meetings upon the request of the chairperson or 1/3 of the members of the board.
3. There shall be a quorum where more than half of the board members are present at a meeting.

፬. ማንኛውም የቦርድ ውሳኔዎች የሚተላለፉት በስብሰባው ላይ ከተገኙት አባላት በድምጽ ብልጫ ሆኖ ድምጹ እኩል ከሆነ የቦርዱ ሰብሳቢ የደገፈው ወገን ሀሳብ የቦርዱ ውሳኔ ይሆናል፡፡

፭. ቦርዱ የራሱ የስነ ስርዓት መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

## ፲፩. <u>የጽህፈት ቤቱ ዋና ስራ አስኪያጅ ተግባርና ኃላፊነት</u>

፩. ፕሮጀክት ጽህፈት ቤቱን በበላይነት ይመራል፣ የፕሮጀክቱን የትግበራ እንቅስቃሴዎች ያቅዳል፤ በመቀመርም ይተገብራል፡፡

፪. የፕሮጀክት አላማዎች፣ ጊዜ ሰሌዳ፣ ባጀት በግራፍ ላይ ግልፅ በሆነ ቦታ እንዲለጠፍ ያደርጋል፡ የቴክኒክ ሰነድ ያዘጋጃል፡፡

፫. የፕሮጀክት አመራር እቅስቃሴዎች ያቅዳል፣ ይፈጽማል፣ የዲዛይን አላማዎች ጊዜ ሰሌዳ እና በጀት በመስራት ሰነድ በማዘጋጀት እቅድ እና የአፈጻጸም ሪፖርት ለቦርዱ ያቀርባል፡፡

፬. የፕሮጀክት ሪከርድ በመስፈርቱ መሠረት መፈጸሙን እና የቴክኒክ ውል ሰነድ መኖሩን ያረጋግጣል፡፡

4. Any decisions of the board shall be passed by the majority vote of the members presented at a meeting. However, in case of a tie, the proposal supported by the chairperson shall be the decision of the board.
5. The board may issue its own rules of procedure.

## 11. <u>Duties and Responsibilities of the General Manager of the Project Office</u>

1. Direct the project office as a head; plan, compose and implement operational activities of the project.
2. Cause the posting of the objectives, time table and budget of the project in a clear position using graph; prepare a technical document.
3. Plan, establish and implement activities of project management; carry out the objectives, time table and budget of the design; prepare and present plan and performance report about it.
4. Make sure the presence of the technical contract document by performing based on the criteria in the project record.

፭. ከኤጀንሲው ዋና ስራ አስኪያጅ ጋር በመመካከር የፕሮጀክት ፅ/ቤቱን አላማዎች፣ ተቀዳሚዎች እና ባጀት ከጊዜ ሰሌዳ ጋር በተመሳከረ ሁኔታ ውጤታማ መሆናቸውን ያረጋግጣል፡፡

፮. የፕሮጀክቱ ተግባራት ጥራት፣ የጊዜ ሰሌዳ እና ወጪ ቁጥጥር ከፕሮጀክት ተቆጣጣሪ ጋር በጋራ ይሰራል፡፡

፯. በመደበኛነት ለኤጀንሲው ዋ/ስራ አስኪያጅ፣ ተቆጣጣሪ ኮሚቴ እና ሌላ የከተማ ድርጅቶች ስለፕሮጀክቱ ሁኔታ እና ሌሎች ስራዎች ሪፖርት በማድረግ ተወያይቶ የፕሮጀክት አገልግሎት በማሻሻል፣ ሲጸድቅ ይተገብራል፡፡

፰. ለፕሮጀክት ፅህፈት ቤቱ የሚያስፈልገውን አመታዊ የስራ እቅድና በጀት አዘጋጅቶ በቦርዱ እንዲፀድቅ ያደርጋል፤ ሲፀድቅም ተግባራዊነቱን ይከታተላል፡፡

፱. የውጭ አማካሪዎች በመቅጠር የሚሰሩትን ስራ ይቆጣጠራል፣ ዲዛይን እና የአፈጻጸም ሁኔታዎችን ከአማካሪ ድርጅቶች ጋር በመዋዋል አስፈላጊውን ይፈጽማል፡፡

፲. በበጀት ዝግጅት እና አስተዳደር ላይ በመሳተፍ የዋጋ ግምት፣ አቅርቦት እና የመሳሪያ ፍላጎት ወጪዎች ማብራሪያ ይሰጣል፡፡

5. Make sure whether the objectives, priorities, and budget of the project office are effective or not with that of the schedule having a discussion with the general manager of the agency or the screening committee.

6. Work closely with the project controller through checking the quality of the project activities, time table and expenses.

7. Perform for the improvement of the services of the project by discussing and reporting the condition of the project and other works for the general manager of the agency regularly; for the controlling committee and other organizations of the city; and implement it upon its approval.

8. Prepare and cause the approval of the annual work plan and necessary budget of the project office by the board; and follow-up its implementation upon approval.

9. Hire external consultants and monitor their activities; carry out the design and implementation conditions through dealing the necessary activities with consultancy organizations based on a contract.

10. Give an explanation about price estimation, supplies and material demands in participating at the budget preparation and administration.

፲፩. ለፕሮጀክቱ አፈጻጸም ተገቢ የሆነ ህግ፣ ደንብ እና ውል ይተገብራል፡፡

፲፪. የፕሮጀክት ስራውን በተመለከተ ለከተማው ምክር ቤት፤ ለቦርዱ እና ለእቅድ ኮሚሽኑ በየሩብ አመቱ ሪፖርት በማዘጋጀት ያቀርባል፡፡

፲፫. ሰራተኞችን ይቀጥራል፣ ይመድባል፣ ያሰናብታል፡፡

## □□ል ሶስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### ፲፪. የመተባበር ግዴታ

ማንኛውም ሰው ይህን ደንብ ሥራ ላይ ለማዋል የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

### ፲፫. የፕሮጀክ ጽህፈት ቤት የቆይታ ጊዜ

፩. የፕሮጀክቱ የቆይታ ጊዜ ሦስት ዓመት ሲሆን እንደአስፈላጊነቱ በካቢኔ ውሳኔ ይራዘማል፡፡

፪. ይህ ጊዜ ሲጠናቀቅ መብትና ግዴታውም ለአዲስ አበባ ከተማ ውበትና መናፈሻ ዘላቂ ማረፊያ ልማትና አስተዳደር ኤጀንሲ ይተላለፋል፡፡

፫. የዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ ፩ እንደተጠበቀ ሆኖ ካቢኔው አስፈላጊ ሆኖ ካገኘው ሁለት ዓመት ሊጨምር ይችላል፡፡

### ፲፬. ሂሳብ አያያዝና ኦዲት

፩. ተቋሙ የሚከተለው የመንግስት የሒሳብ አያያዝ ስርዓት ይሆናል፤

፪. የተቋሙ የሂሳብ እንቅስቃሴና ሃብት ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ ኦዲት ይደረጋል፤

11. Carry out the relevant laws, regulations and contract for the implementation of the project.
12. Prepare a quarterly report and present it to the city council, the board and plan commission.
13. Dismiss, appoint and hire employees.

## Part Three

## Miscellaneous Provisions

### 12. Duty to cooperate

Any person shall be bound to cooperate so as to implement this regulation.

### 13. Duration of the project office

1. The duration of the project office shall three years, if necessary shall be extended by the cabinet decision.
2. The rights and obligation of it shall be transferred to the beautification, parks and cemetery development and administration agency of the Addis Ababa city upon the time ceases.
3. Without prejudice to sub-article of this article city government cabinet may extend two years.

### 14. Account Records and Audit

1. The institution shall follow the account recording system of the government.
2. The capital and financial activities of the institution shall be audited at least once in a year.

**፲፭. ደንቡን ስለማሻሻል**

ይህን ደንብ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ካቢኔ እአንደአስፈላጊነቱ ሊያሻሽለው ይችላል፡፡

**፲፮. መመሪ□ የማውጣት ስልጣን**

የዚህን ደንብ ድንጋጌዎች ለማስፈፀም የሚረዳ መመሪያ ኤጀንሲው ሊያወጣ ይችላል፡፡

**፲፯. ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው ህጎች**

ከዚህ ደንብ ጋር የሚቃረን ማንኛውም ደንብ መመሪያ ወይም አሰራር በዚህ ደንብ ውስጥ በተሸፈኑት ጉዳዩች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

**፲፰. ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ ደንብ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ካቢኔ ከፀደቀበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ**
**ታህሳስ ፲፫ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም**

**ድሪባ ኩማ**
**የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ**

**15. Amendment of the Regulation**

The Addis Ababa city government cabinet may amend this regulation as it may be necessary.

**16. The Power to Issue Directive**

The agency may issue a directive that helps the implementation of the provisions of this regulation.

**17. Inapplicable laws**

Any regulation, directive or any customary practice, which is in consistent with this regulation, shall not be applicable on matters covered under this regulation.

**18. Effective Date**

This regulation shall come into force as of ratification by the Addis Ababa City Government cabinet.

**Done at Addis Ababa**
**This 21st day of January, 2016**

**Diriba Kuma**
**Mayor of Addis Ababa City**